## ክፍል አንድ

## ትምህርት ሦስት

### ► በቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ ከታሪክና ከዓመታትም አኳያ የመጀመሪያዎች ናቸው ተብለው የሚታወቁት የትኞቹ ናቸው?

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያውን ክፍል ይዘው የሚገኙት የሕግ መጻሕፍት ወይም የሙሴ መጻሕፍት ወይም ደግሞ የኦሪት መጻሕፍት(ብሔረ ኦሪት) በመባልየሚታወቁትንነው፡፡ እነዚህም፦ ዘፍጥረት፣ዘጸአት፣ዘሌዋውያን፣ዘኊልቅናዘዳግምናቸው፡፡

### ► ዘፍጥረት ማለት ምን ማለት ነው?

ዘፍጥረትየተባለበትምክንያትስለፍጥረትናየፍጥረትሁሉፍጻሜስለሆነውስለሰውፍጥረትስለሚናገርነው ፡፡ዘፍጥረትስለዓለምአፈጣጠር፣ስለሰውአፈጣጠር፣ እግዚአብሔርከሰውጋርስለመሠረተውቃልኪዳንናሰውበኃጢአት ስለመውደቁ እንዲሁም ስለ ቀደሙት አባቶች አኗኗር ይተርካል፡፡ እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ እንደ ምሳሌው ሲፈጥር ሙሉ ነፃነት ይኖረው ዘንድ እንደወደደ በነፃነቱም ይጠቀም ዘንድ ትእዛዝ እንደሰጠው መጽሐፉ ይናገረናል(ዘፍ 1-2)፡፡ መጽሐፉ እንደሚከተለው ይከፈላል ፦

- **ከምዕራፍ 1-2 ስለ *ሥነ* ፍጥረት ይናገራል፡፡ ከምዕራፍ 3-4 ስለ ሰው ፈተናና ውድቀት ይናገራል፡፡**

**- ከምዕራፍ 5-9 የጥፋት ውሃና የኖኅ ቤተሰቦች ድኅነት፡፡ - ከምዕራፍ 10-11 የዓለም ሕዝብ ትውልድ ዝርዝርና ቋንቋ መለየት፡፡- ከምዕራፍ 12- 23 የአብርሃም ታሪክ፡፡ - ከምዕራፍ 24-26 የይስሐቅ ታሪክ፤- ከምዕራፍ 27-36 የያዕቆብ ታሪክ፡፡- ከምዕራፍ 37-50 የዮሴፍ ታሪክ፡፡**

### ►እግዚአብሔር የሚለው ቃል እንዴት ይገለጻል (እግዚአብሔር ማለት ምን ማለት ነው)? በኦሪት መጻሕፍት ውስጥ ሌሎች መጠርያ ስሞቹስ የትኞቹ ናቸው?

እግዚአብሔርየሚለውቃልየተገኘውከግዕዝሲሆን"እግዚእ"የሚለውጌታማለትነው፤ "ብሔር"ደግሞዓለምበሚለውይተረጐማል፤እግዚአብሔርማለት"የዓለምጌታ"ማለትነው፡፡

በዕብራይስጥእግዚአብሔርየሚጠራባቸውመጽሐፍቅዱስውስጥየተጠቀሱትሦስትስሞችአሉ፡፡

1) **ኤል** ፦ ኃያል (አምላክ) ማለት ነው፡፡ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት "ኤል ወይም ኤሎሂም" የሚለው በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አምላክ፣ አማልክት ተብሎ ብዙ ጊዜ ተተርጕሟል(ዘፍ 1፡ 1፣ መዝ 81፡ 9)፡፡ በዕብራይስጥም ሆነ በሌሎች ሴማውያን ቋንቋዎች የሚናገሩ በእስራኤል አገር በአካባቢዋም ይኖሩ የነበሩ ሁሉ ጣዖቶቻቸውን "ኤል ኤሎሂም" እንደ አማርኛው "አምላክ አማልክት" ብለው ይጠሩአቸው ነበር(ዘጸ 18፡ 11፤ ዘዳ 4፡ 28)፡፡ ከዚህ በተለየ መልኩ ቃሉ ገዥነትን ፈራጅነትንም ስለሚያመለክት ሰዎች ተጠርተውበታል(ዘጸ 7፡ 1፣ ዘጸ 21፡ 6፣ መዝ 82፡ 6፣ ዮሐ 10፡ 34)፡፡ መላእክትም ተጠርተውበታል(መዝ 8፡ 5)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ "ኤል" ከሰውና ከቦታ ስም ጋር ይነገራል፡፡ ለምሳሌ ኤልሳዕ (እግዚአብሔር ደኅንነት ነው)፤ ኤልሳቤጥ (እግዚአብሔር መሐላዬ ነው)፤ ቤቴል (የእግዚአብሔር ቤት)፤ ኤልሻዳይ (ሁሉን ቻይ አምላክ) ማለት ነው (ዘፍ 17፡ 1)፡፡

2) ***ያህዌ*** ፦ አንዳንዶች ይህንን ስም በተሳሳተ መልኩ በመጥራት የሆቫ ወይም የሆዋ በማለት ሲጠሩት ይሰማል፡፡ ያህዌ የእግዚአብሔር ስም ነው፡፡ ትርጓሜውም ያለና የሚኖር እንደ ባሕርዩ

የሚሠራ ማለት ነው(ዘጸ 3፡ 13-15)፡፡ ያህዌ እግዚአብሔር ተብሎ ተተርጕሟል(ዘፍ 4፡ 26)፡፡ ያህዌ ከሌላ ስም ጋር ተዛርፎ ይገኛል፤ ለምሳሌ ያህዌ ይርኤ ማለት እግዚአብሔር ያያል(ዘፍ 22፡ 14)፣ ያህዌ ንሲ "እግዚአብሔር ዓላማዬ ነው" (ዘጸ 17፡ 15)፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ የዚህ ያህዌ የሚለው ስም የቃሉ የመጀመሪያው ክፍል "ያህ" ወይንም "ጃህ" ወይንም "ኢያ" የሚለው ቃል "ያህዌ" የሚለውን ይገልጸዋል ወይንም ያህዌ በሚለው ይተረጐማል፡፡ በዚህም መሠረት የተለያዩ ስሞች ከዚህ ቃል ጋር ተያይዘው እናገኛን፤ ለምሳሌ ኢዮሳፍጥ(እግዚአብሔር ፈርዷል)፣ **ኢዮራም** (እግዚአብሔር ከፍ ከፍ አለ)፣ **ኢያሱ** (እግዚአብሔር አዳኝ)፣ **ሃሌሉያ ሀልሎያህ** (እግዚአብሔርን አመስግኑ) ማለት ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ኤልና ያህዌ በአንድነት ይገኛሉ "እግዚአብሔር አምላክ "ተብለው ይተረጐማሉ(ዘፍ 2፡ 8)፡፡ ኤልያ ማለት "ያህዌ አምላክ ነው" ማለትን ያሳያል ፡፡

3) **አዶን** ፦ አዶን ማለት ጌታ ማለት ሲሆን እንደ አንድ የእግዚአብሔር መጠርያ ስምነት ያገለግላል፤ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ይህንን የዕብራይስጥ ቃል በተለያየ መልኩ ይተረጉመዋል፤ ለምሳሌ "ጌታ" (መዝ 35፡ 23)፣ "እግዚአብሔር"(መዝ 37፡ 13)፣ አቤቱ (መዝ 38፡ 9) ተብሎ ተተርጕሞአል፡፡ አዶን ከልዩ ልዩ ስሞች ጋር ተጣምሮ ይገኛል፤ ለምሳሌ አዶንያስ "ያህዌ" ወይም "እግዚአብሔር ጌታዬ ነው"(2ሳሙ 3፡ 4)፣ አዶኒራም "ጌታዬ ከፍ ያለ ነው"(1 ነገ 4፡ 6)፡፡

**► እግዚአብሔር የባሕርዩ መገለጫዎች የትኞቹ ናቸው?**

የእግዚአብሔርባሕሪ መገለጫዎቹ በትክክልና በተረጋገጠ መልኩ ይህ ነው ለማለት ቢያዳግትም እንደ መጽሐፍ ቅዱሳችን አገላለጽ እግዚአብሔር መንፈስ ነው(ዮሐ 4፡ 24)፤ ብርሃን ነው(1ዮሐ 1፡ 5)፤ ፍቅር ነው(1ዮሐ 4፡ 8)፡፡ እግዚአብሔር አካላዊ ወይም እኔነት ያለው ነውና ራሱን በሚገልጥበት መጠን ልናውቀው እንችላለን (ዮሐ 17፡ 3)፡፡ ነገር ግን የሚሰጠው መገለጥ በከፊል እንጂ ሙሉ በሙሉ እንድናውቀውና እንድናየው አይደለም(ዘጸ 33፡ 20፤ ኢሳ 55፡ 8-9 1ጢሞ 6፡ 16)፡፡ እግዚአብሔር ስለ ራሱ ብዙ ነገሮች ገልጿል፡፡ እነዚህም ነገሮች የእግዚአብሔር የባሕርይ መገለጫዎች ይባላሉ፡፡

**► የእግዚአብሔር ባሕርይ መገለጫዎች ከተባሉት ውስጥ በፍጥረት ወይም ከፍጡራን ዘንድ ሊገኙ የማይችሉት የትኞቹ ናቸው?**

1) ሁሉንቻይነቱ፦እግዚአብሔርለባሕርዩመነሻምክንያትየለውም፤ከዚህተገኘአይባልም፡፡ራሱ በራሱ የነበረ፣ ያለና የሚኖር ነው፡፡ "ያህዌ" የሚለው ስሙም ይህን ይገልጣል(ዳን 4፡ 35፣ ዮሐ 5፡ 26፤ ራእ 4፡ 10-11)፡፡

2) አለመለወጡ፦እግዚአብሔርከዘለዓለምእስከዘለዓለምያውነው፡፡አሳቡምአይለወጥም(መዝ 33፡ 11፤ ሚል 3፡ 6 ዕብ 6፡ 17)፡፡

3) አለመወሰኑ፦እግዚአብሔርበሁሉይገኛል፤መጀመሪያናመጨረሻየለውም(መዝ 145፡ 3፣ 139፡ 7-10፣ ሐዋ 17፡ 27-28)፡፡

4) አለመከፋፈሉ፦እግዚአብሔርከፍጥረቱየተለየነው፡፡ሆኖምበፍጥረትምየሚገኘውሁሉየእርሱሥራነው፡፡ እግዚአብሔርበራሱመንፈስ፣ፍቅርነው(ዮሐ 4፡ 24)፤ ስለዚህሰውወደእግዚአብሔርሲቀርብየባሕርዩመገለጫወደሆኑትወደፍቅሩናወደመንፈሱወደጽድቁምይቀርባል፡፡

ከዚህ በታች የተጠቀሱት ግን በመጠኑ በፍጥረት (በፍጡራን ዘንድ) ያገኛሉ ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን በምልአት ይገኛሉ፤ በክርስቶስም ተገልጠዋል(1 ዮሐ 1፡ 14፤ ቆላ 2፡ 9)፡፡

5) የእግዚአብሔርዕውቀት፦እግዚአብሔርራሱን(1 ቆሮ 2፡ 10)፣በሰውልብያለውን(ሕዝ 11፡ 5)፣ የሚመጣውንም(ኢሳ 46፡ 10) ያውቃል፡፡

6) የእግዚአብሔርጥበብ፦እግዚአብሔርለራሱክብርእንዲሆንሁሉንያደርጋል (ዳን 2፡ 20-21፣ሮሜ 11፡ 33፤ 1 ቆሮ 2፡ 7)፡፡

7) የእግዚአብሔርቸርነት፦እግዚአብሔርለፍጥረትሁሉመልካምነገርንያደርጋል(መዝ 146፡ 8-9፤ማቴ 5፡ 44-45)፡፡

8) የእግዚአብሔርፍቅር፦አብወልድንይወዳል (ዮሐ 10፡ 17)፣ዓለምንምወድዶልጁንሰጠ (ዮሐ 3፡ 16)፡፡ የእግዚአብሔርፍቅርበሦስትቃላትይገለጻል፦

- **ጸጋ፦** በሰው ምክንያት ሳይሆን እንዲሁ በጸጋው እንደሚወድ ያሳያል(ኤፌ 1፡ 6-7)፡፡
- **ምሕረት፦** በኃጢአት ሙታን ስንሆን በምሕረቱ በክርስቶስ ሕይወት ስለሰጠን ፍቅሩን ያሳያል (ኤፌ 2፡ 4-5)፡፡
- **ትዕግሥት፦** ሰዎች እንዲመለሱ በትዕግሥቱ ለንሥሓ ጊዜ በመስጠቱ ፍቅሩን ይገልጣል(ሮሜ 2፡ 4፤ 2ጴጥ 3፡ 9)፡፡

9) የእግዚአብሔር ቅድስና፦ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ የተለየ(ኢሳ 6፡ 3) በራሱም ንጹህ ነው(ዕን 1፡ 13)፤

10) የእግዚአብሔር ጽድቅ፦ እግዚአብሔር ለሰው እንደ ሥራው ይሰጣል(1ጴጥ 1፡ 17)፡፡ ሰውም ለማዳን የኃጢአትን ዕዳ በክርስቶስ በመክፈሉ ጽድቁን አሳየ(ሮሜ 3፡ 26)፡፡

11) የእግዚአብሔርታማኝነት፦እግዚአብሔርታማኝነውና(ዮሐ 14፡ 6) ሐሰትንአይናገርም (ዘኁ 23፡ 19)፤ ቃሉንምይፈጽማል(2ጢሞ 2፡ 13፤ዕብ 10፡ 23)፡፡

12) የእግዚአብሔር ሥልጣን፦ እግዚአብሔር እንደ ባሕርዩ የፈለገውን ለማድረግ ይችላል(ማቴ 19፡ 26)፤ እንደ ፈቃዱም ያደርጋል(ሮሜ 9፡ 14-15፤ ኤፌ 1፡ 11)፡፡

### ► ኃጢአት ምንድን ነው? ከፍጥረት አጀማመር ጋር ሲታይ እንዴትስ ወደ ዓለም ሊገባ ቻለ?

ኃጢአት ማለት ስሕተት፣ ክፋት፣ ሕግን መተላለፍ፣ ዐመፃ፣ በጎ ማድረግን ዐውቆ አለመሥራት፣ በእምነት መሠረት አለመኖር፣ ወደ እግዚአብሔር ክብር አለመብቃት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል(ሮሜ 3፡ 11፤ ሮሜ 12፡ 23፤ 14፡ 23፤ 1ዮሐ 3፡ 4፤ ያዕ 2፡ 10፤ ያዕ 4፡ 17)፡፡ ሰው ኃጢአተኛ በመሆኑ ፍጹም ደግነትን ማሳየት አይችልም፤ በራሱም ወደ እውነት ሊመለስ አይችልም፤ አያስተውልም(1ቆሮ 2፡ 14)፤ አይታዘዝም(ሮሜ 8፡ 7)፤ አያምንም(ዮሐ 6 44-45)፡፡

የመጀመሪያው ሰው አዳም በነፃነቱ ተጠቅሞ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ማፍረስ መረጠ፤ የተከለከለውን ፍሬ ዐውቆ በመብላቱ የእግዚአብሔርን ሥልጣን ተቃወመ፤ ቸርነቱን ረሳ፤ ጸጋውን ናቀ፤ ጥበቡን ነቀፈ፤ ጽድቁን ካደ፤ቃሉንም አቃለለ(ዘፍ 3፡ 1-6)፡፡ በዚህም ምክንያት ሰው ኃጢአተኛ ሆነ፤ ረከሰ፤ ልቡም ክፉ ሆነ(ዘፍ 8፡ 21)፡፡ ይህንንም በማድረግ ኃጢአት፣ በኃጢአትም ሞት ወደ ዓለም እንዲገባ አደረገ፡፡ የአዳም ኃጢአትም በዘሩ ሁሉ ተቈጠረ(መዝ 14፡ 2-3፤ መክ 7፡ 20፤ ሮሜ 5፡ 12፤ 1ቆሮ 15፤ 22)፡፡

**► በኦሪት ዘፍጥረት አገላለጽ መሠረት ሞት ካለ መታዘዝ በመነጨው በኃጢአት ምክንያት የመጣ ነው ማለት ነውን? የሞት አጀማመርና ኃጢአት የተያያዙ ናቸው ማለት ይቻላልን?**

አዎበእግዚአብሔርመልክእንደምሳሌውበመፈጠሩጥንትለዘለዓለምነዋሪየነበረውሰውሁሉመልካሙምሳ ይቀርሁሉምአሁንሟችእንደሆነእንረዳለን፡፡በአዳምአለመታዘዝምክንያትሞትወደዓለምገባ፤ሞትየኃጢአት ውጤት ነው(ሮሜ 5፡ 12 እና 6፡ 23) ፡፡ ማስተዋል ያለብን ግን አዳም ትሞታለህ በተባለው መሠረት ወዲያው በሥጋ አልሞተም ነገር ግን ከእግዚአብሔር በመንፈስ ተለየ (ዘፍ 2፡ 17፤ 3፡ 8፤ 19፡ 22-24)፡፡ ኃጢአት ግን በዓለም ሁሉ ስለተሰራጨ የአዳም ልጅ ነፍሰ ገዳይ ሆነ፤ በኖኅም ዘመን የሰው ክፋት በምድር ላይ በዛ(ዘፍ 4፡ 1-6)፡፡ እግዚአብሔር የጥፋትን ውሃ አዝንሞ ከኖኅና ከልጆቹ በስተቀር የተፈጠረውን ሁሉ አጠፋ(ዘፍ 6፡ 6-9)፡፡ የኖኅ ልጆች ግን ከቀደሙት ሰዎች የተሻሉ ሳይሆኑ በእግዚአብሔር ላይ ዐመፁ፤ በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ለራሱ የሚሆነውን የተለየ ትውልድ ፈልጎ አብራምን ጠራ(ዘፍ 10-12)፡፡ በአጠቃላይ በአዳም ውድቀት ምክንያት ኃጢአትና ሞት ወደ ሰው ሁሉ ደረሰ፡፡

**► አዳም የሚለው ስም የአንድ ግለ ሰብ መጠርያ ስም ብቻ ነው ወይስ ሰዎችን ሁሉ በመወከል የተገለጸ ስም ነው?**

አዳምማለትከመሬትየተፈጠረማለትነው፡፡ቃሉሰውንወይምሰዎችንሁሉያመለክታል፡፡ ከዚህበላይግንየመጀመሪያውሰውየሚጠራበትስምሆነ(ዘፍ 2፡ 19-25)፡፡ አዳምበእግዚአብሔርመልክተፈጠረ(ዘፍ 1፡ 27)፤ እግዚአብሔርምእንዲያበጃትናእንዲጠብቃትበኤደንገነትአኖረው፡፡የምድርንምፍጥረትእንዲገዛሥልጣንሰጠው፡ ፡ ስለዚህ እንደ ኦሪት ዘፍጥረት አገላለጽ ፈጣሪ አምላክ ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠረ፡፡ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ በማለት አንድነታቸውን ባረከ፡፡ “ብዙ ተባዙ፤ ምድርንም ሙሉአት፤ ግዙአትም” አላቸው(ዘፍ 1፡ 28፤ 2፡ 24)፡፡ አዳምና ሚስቱ ለእግዚአብሔር ስላልታዘዙ ከኤደን ገነት እንዲወጡ ተገደዱ(ዘፍ 3) በማለት አዳም አንድ ሰው ብቻ እንደነበረ ይነግረናል፡፡

ነገር ግን አዳም አንድ ሰው ብቻ ነው የሚያመለክተው ካልን በታሪኩ ሂደት ላይ አንድ ጥያቄ ያስነሣብናል፡፡ ይህም አዳምና ሔዋን ሦስት ልጆች እንደነበራቸው ይታወቃል፡፡ እነዚህም አቤል፣ ቃየል እና ሴት ነበሩ፡፡ ቃየል ወንድሙ አቤልን ገደለው(ዘፍ 4፡ 8)፡፡ ከዚህ በኋላ ቃየል ከእግዚአብሔር ፊት ርቆ ሄደ፤ በዔደን በስተምሥራቅ በሚገኘው በኖድ ምድር ኖረ(ዘፍ 4፡ 16) ይላል፡፡ ከዚያም ከሚስቱ ጋር የግብረ ሥጋ ግኑኝነት አደረገ፤ እርስዋም አረገዘች ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙንም ሔኖክ አሉት(ዘፍ 4፡ 17)፡፡ ታሪኩ እንዲህ ከሆነ ሊነሣ የሚችለው ጥያቄ የቃየል ሚስት ከየት ተገኘች? እግዚአብሔርም ለቃይል እንዲህ አለው “ማንም አይነካህም፤ አንተን የሚገድል ሰባት እጥፍ የበቀል ቅጣት ይደርስበታል” አለው፡፡ ይህ የሚያሳየው በአካባቢው ሌሎች ነዋሪዎች እንደነበሩና በምድር ላይ አዳም፣ ሔዋንና ልጆቻቸው ብቻ እንዳልነበሩ ያስረዳል፡፡ ስለዚህ አዳምና ሔዋን የሰውን ፍጥረት ወክለው የተገለጹ የወንድና የሴት አምሳያዎች ናቸው፡፡ አዳም የሰውን ዘር ወክሎ የሚገኝ መጠርያ ስም ነው፡፡

**► ሔዋን ማለት ምን ማለት ነው? በዘፍጥረት አገላለጽ ሔዋን ማን ናት?**

ሔዋንየሕያዋንሁሉእናትማለትነው፡፡ከላይእንደተገለጸውሔዋንየመጀመርያዋሴትየአዳምሚስትናት፡፡ እግዚአብሔርከአዳምሥጋ ፈጠራት፤ አዳምም በደስታ ተቀበላት(ዘፍ 2፡ 20-25)፤ ሰይጣን በእባብ ምሳሌ አታለላትና የተከለከለውን ፍሬ በላች፤ ፍሬውንም ለአዳም ሰጠች፡፡ በኋላም ስሕተትዋን በእባቡ አማካኝች(ዘፍ 3፡ 1-13)፡፡ በስሕተት ስለወደቀች ለባልዋ እንድትታዘዝ በጭንቅም ልጅ እንድትወልድ ተፈረደባት(ዘፍ 3፡ 16)፡፡ አዳም ግን በእግዚአብሔር ቃል ተስፋ አድርጎ ዘር እንደሚኖራት አመነና ሔዋን ብሎ ሰየማት(ዘፍ 3፡ 15)፡፡ ስለዚህ ከላይ እንደተገለጸው ሔዋን የሕያዋን ሁሉ እናት ከአዳም

ጋር በመሆን ፍጥረትን ሁሉ ወክላ የምትገኝ ነች እንጂ አንዲት ሴት ብቻ(አንዲት ግለሰብ ብቻ) አይደለችም፡፡

**►እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረው በኋላ የነበሩ ሰዎች ረጅም እድሜ ይኖሩ እንደነበር ተገልጿል፤ ለምሳሌ ማቱሳላ ለ969 ዓመታት እንደኖረ ከዘፍጥረት እንረዳለን (ዘፍ 5፡ 25)፤ በኋላ ግን የሰው ዕድሜ ከ70 እስከ 80 ዓመታት ገደማ ተወሰነ፤ ይህ ለውጥ ለምን ወይም በምን ምክንያት ተከሰተ?**

ዕድሜየእግዚአብሔርበረከትነው(መዝ 91፡ 16)፤ እግዚአብሔርንየሚታዘዙየረጅምዕድሜተስፋአላቸው(ዘጸ 20፡ 12)፡፡ በእርግጥበአባቶችዘመንሰዎችብዙዓመታትበሕይወትይኖሩነበር (ዘፍ 5 እናዘዳ 34፡ 7)፤ ነገርግንየሰውዘርበምድርላይእየበዛበሄደጊዜነገሮችተለወጡ፡፡ "የሰው ዘር በምድር ላይ እየበዛ በሄደ ጊዜ ሴቶች ልጆች ተወለዱ፤ በዚያን ጊዜ ልዩ የሆኑ ፍጥረቶች የእነዚህን ሴቶች ልጆች ውበት ተመለከቱ፤ ከመካከላቸውም የሚወዱአቸውን እየመረጡ ወሰዱ፡፡ እግዚአብሔርም ሕይወት ሰጭ የሆነው መንፈሴ ከሰዎች ጋር ለዘላለም አይኖርም፤ ሰዎች ሟቾች ስለሆኑ ከእንግዲህ ወዲያ ከ120 ዓመት የበለጠ አይኖሩም አለ" (ዘፍ 6፡ 1-3)፡፡

**►እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ የተጸጸተበትና ያዘነበት ጊዜ አለን? በመጸጸቱና በማዘኑስ የፈጠራቸው ፍጥረቶች ከምድር ላይ ለማጥፋት የወሰነበት ጊዜ አለን?**

አዎእግዚአብሔርበምድርላይያሉሰዎችሁሉምንያህልዐመፀኞችእንደሆኑናአሳባቸውምዘወትርክፋትብ ቻእንደሆነበተመለከተጊዜሰዎችንበመፍጠሩናበምድርላይእንዲኖሩበማድረጉአዘነ፤እጅግምተጸጸተ፡፡ በዚህምምክንያትእግዚአብሔር"እነርሱን በመፍጠሬ አዝኛለሁ፤ ስለዚህ እነዚህን የፈጠርሁአቸውን ሰዎች፣ እንስሳት፣ በደረታቸው እየተሳቡ የሚንቀሳቀሱ ፍጥረቶችና ወፎችንም ጭምር ከምድር ላይ አጠፋለሁ" አለ (ዘፍ 6፡ 5-8)፡፡ በኖኅ ዘመን የተከሰተውም የጥፋት ውሃ የዚህ ውጤት እንደነበር ይታወቃል፡፡

**►የጥፋት ውሃ ማለት ምን ማለት ነው? እግዚአብሔር የጥፋት ውሃ እንዲደርስ ለምን ፈቀደ?**

የጥፋትውሃማለትበኖኅ ዘመን 40 ቀንና 40 ሌሊት ያለማቋረጥ የዘነበ ዝናብና በዝናቡ ምክንያት ምድርንም ያጥለቀለቃት ውሃ ማለት ነው፡፡ ይህ ውሃ ምድርን ሁሉ ለአንድ ዓመት ያህል ሸፍኖት እንደቆየ ይታወቃል፡፡

የሰው ክፋት ሲበዛ፣ የልቡ አሳብና ምኞት ሲከፋ እግዚአብሔር ሰውን ሊያጠፋ ወሰነ፡፡ እግዚአብሔርም ኖኅን እንዲህ አለው "የሰውን ዘር በምድር ላይ ለማጥፋት ወስኛለሁ፤ ምድር በሰዎች የዐመፅ ሥራ ስለተሞላች ሰዎችን ፈጽሞ ከምድር አጠፋቸዋለሁ"(ዘፍ 6፡ 13)፡፡ ይህም ሆኖ ግን የሰው ዘር በሙሉ ከምድር እንዲጠፋ እግዚአብሔር አልፈቀደም፡፡ በምድር ላይ የተወሰኑት እንዲቀሩ አደረገ፡፡

ኖኅበእግዚአብሔርፊትሞገስንአገኘ፤በእግዚአብሔርምትእዛዝመርከብንሠራ፤ የጥፋትውሃበምድርላይሲመጣኖኅቤተሰቡናወደመርከቡያስገባቸውእንስሳትዳኑ፤ሌሎችግንጠፉ(ዘፍ 7)፡፡ ከጥፋት ውሃ በኋላ እግዚአብሔር ዓለምን እንደገና በውሃ እንዳያጠፋ ቃል ኪዳን ሰጠ(ዘፍ 8፡ 20 — 9፡ 17)፡፡ እግዚአብሔርም እንዲህ አለ "ሰው በሚፈጽመው በደል ሁሉ ከእንግዲህ ወዲህ ምድርን አልረግምም፤ ምክንያቱም ገና ከሕፃንነቱ ጊዜ ጀምሮ የሰው አሳብ ክፉ መሆኑን ዐውቃለሁ፤ በአሁኑ ጊዜ እንዳደረግሁት ሕይወት ያለውን ፍጥረት ሁሉ ከእንግዲህ ወዲህ ከቶ አላጠፋም"(8፡ 21)፡፡

**►እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ሰጠ ወይም ቃል ኪዳን ገባ ስንል ምን ማለት ነው? ቃል ኪዳኑ ምንን በተመለከተ ነው? ቃል ኪዳን የተሰጣቸው ወይም የተገባላቸውስ እነማን ናቸው?**

ቃልኪዳንማለትሁለትወይምከሁለትበላይየሆኑሰዎችሲስማሙነገሩንለማጽናትቃልኪዳንይገባባሉ፤ ለምሳሌዮናታንከዳዊትጋርቃልኪዳንገባ(1ሳሙ 18፡ 3-4)። እግዚአብሔርዓለምንናሕዝቡንየሚያስተዳድረውበቃል ኪዳን ሥርዓት ነው። በማናቸውም ቃል ኪዳን ውስጥ የቃል ኪዳን ሰጪ፣ ተቀባይ፣ የአቀባበል ምልክት፣ ተስፋ፣ የተስፋውም ምልክት ይገኛሉ። እግዚአብሔር በሰው ደግነት ሳይሆን እንዲሁ በጸጋው ቃል ኪዳንን ፈቅዶ ይሰጣል። ሰዎችም ቃል ኪዳኑን ተቀብለው ቢታዘዙለት የቃል ኪዳኑን በረከት ይቀበላሉ።**ቃል ኪዳኑን ሲቀበሉ እግዚአብሔር ምልክት ያበጃል። ይህም የቃል ኪዳኑ ማኅተም ነው። እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ ውስጥ ላሉት ተስፋና የተስፋ ምልክት ይሰጣቸዋል። ስለ ሰው ያለው የእግዚአብሔር አሳብ አይለወጥም።** ከመጀመርያው ጀምሮ ሰውን በጸጋው ተመልክቷል። ከሰው የሚፈለጉት ደግሞ እምነትና መታዘዝ ናቸው። እነዚህ ነገሮች ከዘመን ዘመን አይለወጡም። ዘመን ሲለወጥ የቃል ኪዳኑ ዋና መሠረት አይሰረዝም(ገላ 3፡ 15-18)። ነገር ግን የአፈጻጸሙ ድርጊት ይለወጣል (2ቆሮ 3፡ 6-18፤ ዕብ 8፡ 6-13)።

በተለያዩ ጊዜያት ለተለያዩ ሰዎች እግዚአብሔር የሰጣቸው ቃል ኪዳኖች እስከነ ምልክቶቻቸው እንደሚከተለው ይቀርባሉ ፦

| **የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የተሰጠው** | **ተቀባዮች** | **የመቀበላቸው ምልክት (ማኅተም)** | **ተስፋ** | **የተስፋ ምልክት (ማኅተም)** |
|---|---|---|---|---|
| **ለአዳም** (**ዘፍ** 2፡ 8-17፤ **ሆሴ** 6፡ 7) | አዳምና ሔዋን | መልካምና ክፉን የሚያሳውቅ ዛፍ | ሕይወት | የሕይወት ዛፍ |
| **ለኖኅ** (**ዘፍ** 9፡ 1-17) | የዓለም ሕዝብ | | በምድር መኖር | ቀስተ ደመና |
| **ለአብርሃም** (**ዘፍ** 17፡ 1-21፤ **ሮሜ** 4፡ 11) | አብርሃምና ዘሩ | ግዝረት | የአሕዛብ በረከት፤ የከነዓን ምድር | |
| **ለሙሴ** (**ዘጸ** 19፡ 5፤ 6፡ 24፤ 7፡ 8 | የእስራኤል ሕዝብ | ሰንበት (ሕዝ 20፡ 10-17) | ሕይወት በአገራቸው | የፋሲካ መታሰቢያ |
| **በክርስቶስ** (**ኤር** 31፡ 31-34፤ **1ቆሮ** 11፡ 23-26)፤ | በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ | ጥምቀት | የዘላለም ሕይወት | ቅዱስ ቁርባን |

በአጠቃላይእግዚአብሔርከአዳም ጋርየሥራቃልኪዳንአደረገ። አዳምቢታዘዝኖሮለእርሱናለዘሩየዘላለምንሕይወትያስገኝነበር፤ ባለመታዘዙግንየኃጢአትንፍርድበእርሱናበዘሩላይአስከተለ (ሮሜ 5፡ 12-21)። ክርስቶስሁለተኛውአዳምስለሆነበእርሱለሚያምኑትሕይወትአስገኝቶላቸዋል (1ቆሮ 15፡ 20 እናከ45-50)።

**የትምህርቱ አዘጋጅ ፦ አባ ምስራቅ ጥዩ**

**የትምህርቱ አስተባባሪ፦ አቶ ተስፋዬ ባደገ**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከመለሱ በኋላ ወደ ሀገረስብከቱ የተልእኮ ትምህርት ዝግጅት ክፍል ይላኩት።

**የተማሪው/ዋ ስም ------------------------------------------ኮድ-------- ቁምስና--------------------ውጤት---------**

1) የሰውናየፍጥረትእንዲሁምሰማይናምድርበውስጥዋምያሉነገሮችሁሉአፈጣጠርበኦሪትዘፍጥረትምዕራፍአን ድና ሁለት ውስጥ ተደጋግሞ ተገልጿል። ለመሆኑ እንደ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ አገላለጽ ሰው በስንተኛው ቀን ተፈጠረ? ምዕራፍ ሁለትስ ውስጥ ሰው የተፈጠረው በመጀመሪያ ነው ወይስ በፍጥረት መጨረሻ ወይስ በፍጥረት መካከል?

2) የሰውአፈጣጠርበኦሪትዘፍጥረትምዕራፍአንድናምዕራፍሁለትውስጥየተለያየነው፤ ይህንየሰውአፈጣጠርበተመለከተከሚከተሉትውስጥትክክለኛያልሆነውንመልስምረጥ። ሀ)ዘፍጥረት አንድ ላይ ሰው በእግዚአብሔር መልክና አምሳያ ተፈጠረ፤ ለ)ዘፍጥረት አንድ ላይ እግዚአብሔር ሰዎችን ሲፈጥራቸው ወንድና ሴት አድርጎ ነው፤ ሐ)ዘፍጥረት ሁለት ላይ እግዚአብሔር ከመሬት ዐፈር ወስዶ ሰውን ከዐፈር አበጀው፤ መ)ዘፍጥረት ሁለት ላይ እግዚአብሔር በመጀመሪያ አዳም ፈጠረ፤ ቀጥሎም ከጎኑ አጥንት አንዱን ወስዶ ሴት አድርጎ ሠራት፤ ሠ)ሁሉም ትክክል ናቸው።

3) እግዚአብሔርአምላክ ሰውን ከፈጠረው በኋላ በዔደን ገነት አኖረው፤ ቀጥሎም ሰውን "በአትክልቱ ቦታ ከሚገኙ ዛፎች ሁሉ ፍሬ ልትበላ ትችላለህ፤ ነገር ግን ደጉን ከክፉ ለመለየት የሚያስችል ዕውቀት ከሚሰጠው ዛፍ ፍሬ አትብላ" አለው(ዘፍ 2፡ 15-17)። ሴቲቱም (ሔዋን) እባቡ ፍሬውን ወስዳ እንድትበላ በተናገራት ጊዜ "እግዚአብሔር በአትክልቱ ቦታ መካከል ካለው ዛፍ ፍሬ አትብሉ፤ በእጃችሁም አትንኩት፤ ይህን ብታደርጉ ትሞታላችሁ" ብላ መለሰችለት። በዚህ ጊዜ እባቡ ሔዋንን ለማሳሳት የተናገራት ንግግር ምን ነበር? (ዘፍ 3 አንብብ)

4) በመጽሐፍ ታሪክ ውስጥ አቤልና ቃየል ከሚታወቁባቸው ነገሮች ውስጥ ትክክለኛ ያልሆነውን ምረጥ፤ ሀ)ለመጀመሪያ ጊዜ ለእግዚአብሔር መባ ወይም መሥዋዕት ያቀረቡ ናቸው፤ ለ)ለመጀመሪያ ጊዜ የግድያ ታሪክ እርስ በርሳቸው የፈጸሙ ናቸው፤ ሐ)ለመጀመሪያ ጊዜ ወንድም በወንድሙ ላይ የጭካኔ ተግባር ከመፈጸም ጋር የሚጠቀሱ ናቸው፤ መ)ለመጀመሪያ ጊዜ ከሰው ዘር የተወለዱ ናቸው፤ ሠ)ለመጀመሪያ ጊዜ በእግዚአብሔር የተረገሙ ናቸው።

5) የአዳም ዝርያዎች ስም ዝርዝር በምናይበት ጊዜ ከአዳም ጀምሮ እስከ ኖኅ ድረስ ዐሥር ትውልድ እንደሆነ እንረዳለን(ዘፍ 5)። በአዳምና በኖኅ መካከል ያሉት በስምንት ሰዎች የተገለጹት ስምንት ትውልዶች እነማን ናቸው? ስማቸውና በዚህ ምድር ላይ ለስንት ዓመታት እንደኖሩ ግለጽ።

1) አዳም በዚህ ዓለም የኖረው ለ930 ዓመት ነው።2) ሴት ሲሆን የኖረውም 912 ዓመት ነው።

3) ሄኖስ ሲሆን 905 ዓመት ኖረ።4) ቃይናን የኖረው 910 ዓመት ነው።

5) መላልኤል የኖረውም 895 ዓመት ኖረ።6) ያሬድ የኖረውም 962 ዓመት ነው።

7) ሄኖክ የኖረውም 365 ዓመት ነው። 8)ማቱሳላ የኖረውም 965 ዓመት ነው።

9. ላሜሕ የኖረውም 747 ዓመት ነው። 10) ኖኅ የኖረው ለ950 ዓመት ነው።

## የትምህርት ሦስት መልስ

1. እንደ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ አገላለጽ ሰው በስድስተኛው ቀን ተፈጠረ።
   - እንደ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ሁለት አገላለጽ ሰው በመጀመሪያው ቀን ተፈጠረ።

2. ሠ

3. አባቡም እንዲህ አላት፤ ሞትን አትሞቱም፤ ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዐይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ።

4. ሠ

5. 1)አዳም በዚህ ዓለም የኖረው ለ930 ዓመት ነው። 2) ሴት ሲሆን የኖረውም 912 ዓመት ነው።
   3) ሄኖስ ሲሆን 905 ዓመት ኖረ። 4) ቃይናን የኖረው 910 ዓመት ነው።
   5) መላልኤል የኖረውም 895 ዓመት ኖረ። 6) ያሬድ የኖረውም 962 ዓመት ነው።
   7) ሄኖክ የኖረውም 365 ዓመት ነው። 8)ማቱሳላ የኖረውም 965 ዓመት ነው።
   9. ላሜሕ የኖረውም 747 ዓመት ነው። 10) ኖኅ የኖረው ለ950 ዓመት ነው።